መዘመር ሳሊ
ለለ ነ·ሩ·ን

ዋልያ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ።
አቤቱ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ናፍቃለች።
ነፍሴ ሕያው አምላክን ተጠማች።
መቼ እደርሳለሁ?
የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ?
ዘወትር አምላክህ ወዴት ነው? ሲሉኝ።
እንባዬ በቀንና በሌሊት ምግብ ሆነኝ።
ይህን ባስብሁ ጊዜ ነፍሴ በእኔ ውስጥ ፈሰሰች።
ወደ እግዚአብሔር ቤት የምሰጋና አደራሽ እገባ
ነበርና።
በዓል የሚያደርጉ ሰዎች የደስታና የምስጋና ቃል
አሰሙ።
ነፍሴ ሆይ ለምን ታዝናለሽ?ለምንስ ታውኪኛለሽ?
የፊቴን መድኃኒት አምላኬን።
አመሰግነው ዘንድ በእግዚአብሔር ታመኚ።
አምላኬ ሆይ ነፍሴ በእኔ ውስጥ ታወከች።
ስለዚህ በዮርዳኖስ ምድር በአርሞንኤምም በታናሹ
ተራራ አስብሃለሁ።
በሃይቴህ ድምፅ ወንዝ ወንዝን ተጠራታለች።
ማዕበልህና ሞገድህ ሁሉ በላዬ አለፈ።

Scanned with CamScanner

እግዚአብሔር በቀን ቸርነቱን ያዝዛል፤ በሌሊትም
ዝማሬው በእኔ ዘንድ ይሆናል።
የእኔ ስእለት ለሕይወቴ አምላክ ነው።
እግዚአብሔርን አንተ መጠጊያዬ ነህ ለምን
ረሳኸኝ?
ጠላቶቼ ሲያስጨንቁኝ።
ለምን አዘኔ እመላለሳለሁ? እለዋለሁ።
ጠላቶቼ ሁል ጊዜ አምላክህ ወዴት ነው? ባሉኝ
ጊዜ።
አጥንቶቼን እየቀለጣጠሙ ሰደቡኝ።
ነፍሴ ሆይ ለምን ታዝኛለሽ? ለምንስ ታውኪ
ኛለሽ?
የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ
በእግዚአብሔር ታመኚ።

Scanned with CamScanner


መዝሙር ፶፱
ስለ ትሩፋን

አቤቱ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ።
እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ።
ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ።
ከኃጢአቴም አንጻኝ።
እኔ መተላለፌን አውቃለሁና።
ኃጢአቴም ሁል ጊዜ በፊቴ ነውና።
አንተን ብቻ በደልሁ፤ በፊትህም ክፋትን አደ
ረግሁ።
በነገርህ ትጸድቅ ዘንድ በፍርድህም ንጹሕ ትሆን
ዘንድ። እነሆ በዓመፃ ተፀነስሁ።
እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ።
እነሆ እውነትን ወደድህ።
የማይታይ ስውር ጥበብን አስታወቅኸኝ።
በሂሶጵ እርጨኝ፤ እነጻማለሁ።
እጠበኝ፤ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ።
ሐሜትንና ደስታን አሰማኝ።
የሰበርሃቸውም አጥንቶቼ ደስ ይላቸዋል።
ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ።
በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ።
አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ።

Scanned with CamScanner

ቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።
ከፊትህ አትጣለኝ።
ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ።
የማዳንህን ደስታ ስጠኝ።
በጽኑ መንፈስም ደግፈኝ።
ለሕግ ተላላፎች መንገድህን አስተምራለሁ።
ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ።
የመድኃኒቴ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ ከደም
አድነኝ።
አንደበቴም በአንተ ጽድቅ ትደሰታለች።
አፌ ምስጋናህን ይናገር ዘንድ አቤቱ ከንፈሮቼን
ክፈት።
መሥዋዕትን ብትወድስ በሰጠሁህ ነበር።
የሚቃጠለውም መሥዋዕት ደስ አያሰኝህም።
የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ
ነውና። የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብ
ሔር አይንቅም።
አቤቱ በውዴታህ ጽዮንን አሰማምራት።
የኢየሩሳሌምንም ቅጽሮች ሥራ።
የጽድቁን መሥዋዕት መባውንም የሚቃጠለውንም
መሥዋዕት በወደድህ ጊዜ።
ያን ጊዜ በመሠዊያህ ላይ ፍሪዳዎችን ይሠዋሉ።

Scanned with CamScanner


ይሁን። የእ[illegible]

መዝሙር ፯

ስለ ሕገ-ቅዳሴ

በልዑል መጠጊያ የሚኖር።
ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል።
እግዚአብሔርን አንተ መታመኛዬ ነህ አለዋለሁ።
አምላኬና መሸሸጊያዬ ነው፤ በእርሱም
እታመናለሁ። እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ከሚያስደነ
ግጥም ነገር ያድነኛልና።

Scanned with CamScanner

በላባዎቹ ይጋርድሃል።
በክንፎቹም ጥላ ትጠለላለህ።
እውነት እንደ ጋሻ ይከብሃል።
ከሌሊት ግርማ በቀን ከሚበር ፍላጻ።
በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር።
ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም።
በአጠገብህ ሺህ።
በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ።
ወደ አንተ ግን አይቀርቡም።
በዓይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ።
የኃጥኣንንም ብድራት ታያለህ።
አቤቱ አንተ ተስፋዬ ነህና።
ልዑልን መጠጊያህ አደረግህ።
ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም።
መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም።
በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ።
መላእክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋልና።
እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል።
በእጆቻቸው ያነሡሃል።
በተኩላና በእባብ ላይ ትጫማለህ።
አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ።
በእኔ ተማምኗልና አስጥለዋለሁ።

ስሜንም አውቄልና እጋርደዋለሁ።
ይጠራኛል፤ እመልስለትማለሁ።
በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋራ እሆናለሁ።
አድነዋለሁ፤ አከብረዋማለሁ።
ረጅምን ዕድሜ እሰጠዋለሁ።
ማዳኔንም አሳየዋለሁ።

Scanned with CamScanner